5ኛ ክፍል ስነ-ዜጋና ስነ-ምግባር



የክለሳ ማስታወሻ

አዘጋጅ፡ አብዱ አሊ

መስከረም
2013

ምዕራፍ ሰባት
ጠንካራ የስራ ባህል

- ስራን መፍጠር
- ስራን መፍጠር ማለት ምን ማለት ነው?
- ሁሉም ሰው የፈለገውን የስራ ዓይነት በመፍጠር ና በማሻሻል ወደ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለመደረስ ይችላ።አንድ ሰው ስራን ፈጥሮ ለመስራት ከሚያስፈልጉት መሰረታዊ ነጥቦች መካከል፦
- የስራ ክቡርነትን መረዳት
- የስራ ተነሳሽነት
- ጥረትን ማዳበር ማንኛውም ስራ ክቡር ነው።

- **ሳይሰሩ መብለት**
- ሳይሰሩ መብላት ማለት ምን ማለት ነው? ሳይሰሩ መብላት ማለት ሌሎች ሰዎች በለፉትና በደከሙበት ውጤት መጠቀም ማለት ነው።
- ማንም ሰው በቤተሰቡም ይሁን በህበረተሰቡ አባልነቱ ስራ ካልሰራ የሌሎች ሸክም ሆነ ማለት ነው።
- **ሳይሰሩ መብላት ከሚያስከትሉአቸው ችግሮች ውስጥ**
- ስራ ለሰው ልጅ የመኖር ዋስትና ነው።
- ሁሉም ሰው በአቅሙና በችሎታው ለመስራት ካልተጣጣረ የሰዎች የኑሮ ሁኔታ ሊሻሻል አይችልም።
- የሀገር እድገትም አይኖርም
- ጥገኝነት ይስፋፋል
- ጥገኝነት ማለት የሌሎችን እጅ በመጠበቅ ግልፅ ከመብት ሀብት መኖር ማለት ነው።
- ሰው መኖር ያለበት አቅምና ችሎታው በሚፈቅደው ስራ ላይ ተሰማርቶ በሚያስገኘው ውጤት መሆን ይገባዋል።

ህገ መንግስታዊ የስራ መብቶች

- ስራ አየሰሩ መኖር የሁሉም ዜጎች መብት ነው።
- ህፃናት በሚችሉት የስራ አይነት መሳተፋቸው ጥሩ ነው።
- የመስራት መብት የተነፈገ ሰው የመኖር መብቱንም ተነፍጓል ማለት ነው።
- ምክንያቱም የሰው ልጅ ኑሮና ስራ የማይነጣጠሉ በመሆናቸው ነው።

የፈለጉትን ስራ በፈለጉት ቦታ የመስራት መብት

- ለሁሉም ዜጎች የተፈቀደው ና በህገመንግስቱ የተቀመጠው የመስራት መብት ህገ መንግስታዊ የመስራት መብት በመባል ይታወቃል። ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ናቸው
- ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፈለገውና የመረጠውን አይነት ስራ የመስራት መብት አለው።
- ማንኛውም ሰው ሙያውን የመምረጥና ወደፈለገው ቦታ ሄዶ የመስራት መብት አለው።
- ማንኛውም ሰው የግል ንብረት የማፍራት ና የባለቤትነት መብት አለው።

- **ሙያና የሙያ ስነ-ምግባር ምንነት**
- ሙያ የራሱ የሆነ ልዩ ዕውቀትና ችሎታን የሚጠይቅ የስራ አይነት ነው። ለምሳሌ ግብር፣ጋዜጠኝነት፣መምህርነት፣ዳኝነት የመሳሰሉት የሙያ አይነቶች ናቸው።
- የሙያ ችሎታ ማለት በአንድ ስታ ላይ ለመሰማራት የሚያስችል ና ስለዚያ ሙያ ሊኖረን የሚገባው ዕውቀትና ችሎታ መኖር ማለት ነው።
- የሙያ ስነ-ምግባር ማለት ደግሞ አንድ ሙያ በተግባር ላይ ሲውል ባለሙያው ሊያከብረው የሚገባው የሙያው ደንብና የአሰራር ስርዓት ነው።

- **ለሙያው ደንብና የስራ መሮሆች መገዛት**
- አንድ ባለሙያ የሚሰራው ስራ ውጤታማ ይሆን ዘንድ አስቀድሞ የዚያን የሞያ ስራ ስነስርዓቶችን በሚገባ ማወቅ ይኖርበታል።
- አንድ ስራ ጥሩ ውጤት የሚኖረው ባለሙያው ራሱ ሙያውን ለማሳደግ በሚያረገው ጥረት ነው።
- ህዝብን በቅንነት በታማኝነትና በመልካም ሙያዊ ስነ-ምግባር ማገልገል ደግሞ ሀገርን ወደ ላማትና እድገት ያሸጋግራል።

- **ራስን የመቻል ምንነት**
- ራስን መቻል ማለት የራስን ጉልበትና አቅም ጠንቅቆ በማወቅ በዚያው መጠን የሚቻለውን ነገር ሁሉ በራስ ተነሳሽነት ጠንክሮ መስራት ነው።
- የራስን መቻል መገለጫዎች
- በራስ መተማመን
- ራስን መሆን
- የሌሎችን ሀሳብ ማክበር
- ችግር ፈቺ መሆን
- ለላቀ ስራ ክብር መስጠት
- ችሎታን ማወቅ

በራስ መተማመን

- በራስ መተማመን ማለት የራስን አቅም ጠንቅቆ በማወቅ በሚሰሩት ስራ ላይ እርግጠኛ መሆን መቻል ነው።
- በራስ ለመተማመን ጠንክሮ መስራትና እውቀትን ማዳበር መሰረታዊ ነገሮች ናቸው።
- በአቋም መፅናት
- ማንኛውም ሰው አንድን ጉዳይ ለመፈፀም ቆርጦ መነሳቱን ሲገለፅ አቋም ይዟል ይባላል።

- **ለራሳችን ለሚኖረን ተሳሳተ ግንዛቤ የሚገለፅባቸው ባህሪያት**
- የበላይነት ስሜት
- **የበላይነት ስሜት ራስን ብቻ ከፍ አድርጎ ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ከመመልከት የሚመነጭ ነው።**
- **የበታችነት ስሜት**
- የበታችንነት ስሜት የሚመነጨው ራስን ዝቅ አድርጎ ከመመልከት ነው።
- ለሀገር እድገትና ብልፅግና መስራት
- ሀገራችንን ማሳደግና ማበልፀግ የምንችለው በልማት ስራዎች ላይ ሁሉ ተጋግዘን በአንድ መንፈስ ስንሰራ ብቻ ነው።
- ለሀገር እድገትና ብልፅግና ከሚጎዱ ተግባራት

ኮንትሮባንድ

- **ኮንትሮባንድ** ማለት ከሁለት የጣሊያንኛ ቃላት የተመሰረተ ነው። <<ኮንትራ>> ማለት መቃወም፣መፃረር እና ተቃራኒ መሆን ማለት ሲሆን <<ባንድ ማለት አዋጅ ህግንና መመሪያን ያጠቃልላል።
- የኮንትሮባንድ ንግድ ማለት ህግንና መመሪያን በመተላለፍ በመቃወም የሚደረግ የንግድ እንቅስቃሴ ነው።

- በአጠቃላይ ኮንትሮባንድ በአሁኑ ጊዜ ድርጊቱም፦
- ለሽብርተኝነት የገንዘብ ምንጭ በመሆን ያገለግላል፣
- የመንግስት ገቢን ያሳጣል
- ጥራትና ደረጃውን ያልጠበቀ ሸቀጦች እና ያልተፈቀዱ የጦር መሳሪያዎች ወደ ሀገር እንዲገቡ በማድረግ የሀገርን ሰላምና ኢኮኖሚ፣ የህዝብና ማህበራዊ ህይወት እና ጤናን በማቃወስ ላይ የሚገኝ ከባድ ወንጀል ነው።